# ወኔ ካለንማ!

ከአንሙት

ጠላቱን ለብላቢ፣ አንፋሪ እንደማማ፣
እልህ የሚወጣ፣ ወኔ ካለንማ፣
ማይሆን እህት እናት፣
እስኪ ያገር ጠላት፣ ተቃጠለ እንስማ!

ያገር ፍሬ ልጆች፣ በምትወልደው እህት፣
ያገር ፍሬ ልጆች፣ በምትወልደው እናት፣
ውለታ በል ሆነን፣ ከምናፈስባት፣
አካሏን አቃጥለን፣ በጀብድ ልናጠፋት፤
እስኪ ያገርን መርዝ፣ በመርዙ እንመርዘው፣
አረም ጨጎጌቱን፣ ከምርት ልንለየው!

ወኔ ያለውማ፣ መርዝ ለጠላቱ፣
መቼ ይደፋዋል፣ በእህቱ፣ በእናቱ፣
ከልኩ ሲያልፍበት፣ ግፍና ጥቃቱ፣
ያደርገዋል እንጂ፣ የፈውስ መገኛ ዋና መዲሃኒቱ፣
ጨቋኝ አምባገነን የሚያቃጥልበት፣ የሚያነዱበቱ!

ወኔ ካለንማ፣ ፈንቅሎ እሚወጣ!
እናቶችን ገድሎ፣
እህቶችን ገድሎ፣
ለጋ ህፃናትን፣ ወላጅ ከሚያሳጣ፣
ለምንድነው ከቶ፣ ያገር ፀር ወያኔን፣ አቃጥሎ እማይቀጣ?!

ለምን ይቃጠላል፣ ባሲድ የእናት ገላ?!
ለምን ይቃጠላል፣ ባሲድ የእህት ገላ?!
ስንት ቆሻሻ እያለ፣ የታሪክ አተላ፣
እልህ ቱግ የሚያደርግ፣ ወኔ የሚያፈላ።